
# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአብነት ት/ቤቶች

## ፪.፩ አቋቋም

- ትርጉም፡- የመቆም ሥነሥርዓት፣ የአቋቋም ልክ መልክ የሚነገር ትምህርት ሲሆን በመቋሚያ በከበሮ በጸናጽል አዛምዶና አዋሕዶ በጭብጨባና በእልልታ እየታጀበ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት የቅዱስ የሬድ የዜማ ክፍል ነው::
- በአሁኑ ወቅት የሚታወቁ የአቋቋም ትምህርት ቤቶች፡-
  - ፩ ፡ላይ ቤት
  - ፪ ፡የታች ቤት
  - ፫ ፡የሳንካ
  - ፬ ፡ተክሌ ናቸው






- ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ፡- እስከ ፬ ዓመታት ነው::
- የትምህርቱ መስጫ መጻሕፍት፡- አቋቋም ከነምልክቱ፣ ዚቅወመዝሙር
- ትምህርቱ የሚያካትታቸው፡- የዜማ ምልክት፣የመቋምያ እና የጽናጽል አጣጣል መለየት
- የትምህርቱ ጥቅም፡- በበዓል ጊዜ ሊባሉ የሚያስፈልጉት ዝማሜ /ዘንግ/ ንዑስ መረግድ፣ ዓቢይ መረግድ፣ ድርብ መረግድ፣ ድፋት፣ መልስ፣ ወረብ እንደቅደም ተከተላቸው በማወቅ እግዚአብሔር ይመሰገንበታል::
- ማስመስከሪያ ቦታ፡- ተክሌ (ደቡብ ጎንደር ደብረ ኢየሱስ) ታችቤት ጎንደር በአታ

## ፪.፪ ዝማሬ መዋሥዕት

- ዝማሬ፡- ምስጋና ማለት ሲሆን የሥጋ ወደሙ ሥነ ሥርዓት ከተከናወነ በኋላ ለምሥጢረ ቁርባን የሚዘመር ጎብስት፣ ጽዋዕ፣ መንፈስ፣ አኩቴትና ምሥጢር የተባሉ አምስት ክፍሎችን የያዘ ድርሰት ነው::
- መዋሥዕት፡- አውሥአ መለሰ ካለው ግዕዝ የወጣ ነው:: ለሙታን ጸሎተ ፍትሀት የሚጸለይ ድርሰት ነው:: ከዝማሬ ጋር አብሮ በአንድ ወንበር የሚሰጥ ትምህርት በመሆኑ ዝማሬ መዋሥዕት ተብሎ ይጠራል::
- ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ፡- ፪-፫ ዓመታት
- ትምህርቱ ጥቅም ወይም አገልግሎት፡- ዝማሬ ሥርዓተ ቅዳሴ ተከናውኖ ምስጢረ ቁርባን በሚሰጥበት ጊዜ ከድርገት በኋላ የሚቀርብ ሲሆን ፤መዋሥዕት በጸሎተ ፍትሐት ለሙታን የሚጸለይ ነው::
- ማስመስከሪያ፡- ጽርሐ አርያም ዙር አባ አቡነ አረጋዊ ገዳም ደቡብ ጐንደር::





